ስነ ዜጋና ስነ ምግባር
6ኛ ክፍል

ኑር አፍሪካ አካዳሚ




የክለሳ ማስተዋሻ

አዘጋጅ : አብዱ አሊ
ጥቅምት
2013

ምዕራፍ ዘጠኝ
የቁጠባ ባህል
የቁጠባ ጠቀሜታ

- መሰረታዊ ፍላጎቶችን አሟልቶ ለመኖር
- ያልታሰቡ ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ለመቋቋም
- ራስን ለመቻል
- በራስ የመተማመን ችሎታ እዲኖር ይጠቅማል
- ጥገኝነት ወይም የበታችነት ስሜት እንዳይኖር ይጠቅማል
- በህመምናበእርጅና ወቅት የሌሎችን እጅ ከማየት ያድናል
- ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎች
- አላስፈላጊ ወጪዎችን ማስወገድ ወይም መቀነስ
- ራስንና ቤተሰብን በአቅድና በዓቅም ልክ ማስተዳደር
- ተቀማጭ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግ ወዘተ ናቸው።
- በአካባቢ የቁጠባ ባህልን የሚፃረሩ ተግባራት
- ከአቅም በላይ ድግስ
- ጎለቀር አመለካከት ወዘተ...ናቸው።



ድህነት

የድህነት አስከፊነት

- የገንዘብና የአስተሳሰብ ድህነት የድህነት ሁለት መልክት ናቸው።
- ሁለቱም ጥገኝነትን ይፈጥራሉ። የገንዘብ ድህነት ጠንክሮ በመስራትና በእቅድ በመመራት ሊሸነፍ ይችላል። የአስተሳሰብ ድህነት ሊቀየር የሚችለው መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችለው ትምህርት ብቻ ነው።
- **የአባካኝነትና የድህነት ዝምድና**
- ድህነት ከሚመጣባቸው መንገዶች አንዱ ብኩንነት ነው። ብኩንነት ያለንን ማናቸውንም ገንዘብ ወይም የንብረት አይነት ያለእቅድ ማውጣትና መጠቀም ነው።
- **ድህነትን ለማጥፋት ወጪን መቀነስና ቁጠባን መልመድ**
- ወጪን ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑና አስፈላጊ ያልሆኑ ወጪዎችን ለይቶ ማወቅ ወሳኝ ነው።

ምዕራፍ አስር

ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ

- እያንዳንዱ ዜጋ በፖለቲካዊ፣በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በፍላጎትና በፈቃደኝነት የሚያደርገው የተሳትፎ አይነት ነው። እያንዳንዱ ዜጋ የሚከተሉትን ሀሳቦች እንደመርህ በመጠቀም ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል።
- የመቻቻልን ባህል ማዳበር
- መልካም ስነ ምግባርን መላበስ
- ከሌሎች ጋር በህብረት መስራት
- ለራሱና ለሚሰጠው ስራ ክብር መስጠት
- ቀና ወይም ትሁት መሆን እና ለተነሳለት አላማ ተገዢ መሆን ይኖርበታል።
- በሲቪክ ማህበራት ተደራጅቶ የመሳተፍ ጠቀሜታ
- የሲቪክ ማህበራት የየራሳቸውን የተለያዩ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ይዘው በራስ ተነሳሽነት በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የሚመሰረቱ ማህበራት ናቸው።
- የሲቪክ ማህበራት በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው።
- መንግስት ባለው አቅም ውስን ምክንያት ሊያከናውን በማይችልባቸው መስኮች አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ።
- በሲቪክ ማህበራት ውስጥ ግለሰቦች በአባልነት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ልምድና እውቀት እንዲያገኙ ያስችላል።

ምዕራፍ አስራ አንድ

ዕውቀትን መሻት

- ዕውቀት ከእድሜያችን፣ ከልምዳችንና ከትምህርት ደረጃዎችን በምናገኘው መረጃ ተመስርቶ የሚያደርግ የህሊና ሀብት ነው። እውቀት ከመፅሀፍት፣ከጋዜጦች ፣ከሬድዮና ከቴሌቪዥን እንዲሁም ከሰዎችና ከአካባቢያችን የሚገኝ ነው።
- **የመረጃ ምንጮች**
- ምልከታ(Observation)
- የህትመት ውጤቶች(print media)
- የኤሌክትሪክ ሚዲያ
- **ኃላቀር አስተሳሰብና አመለካከት**
- ኃላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ማለት በሳይንስ ባልተደገፈ ጭፍን ግምት ላይ የተመሰረተ ጎጂ ልማድ ነው።

መረጃ

- መረጃ ስለቤተሰባችን፣ ስለአካባቢያችን፣ስለራሳችን፣ ስለትምህርት ቤታችን እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ስለሀገራችን ጠቃሚ ሀሳቦች የምናገኝበት መንገድ ነው።

የማንበብ ልምድ

- ንባብ ዕውቀታችንን የምናዳብርበት መሣሪያ ነው።

የትምህርት አጠናን ዘዴ

- የጥናት ንባብና ሌላው ንባብ መጠነኛ ልዩነት አላቸው።
- በጥናት ንባብ የትምህርት ነጥቦች እስኪገቡን ድረስ እየመላለስን ማንበብ አለብን።
- **ጥናት የሚከተለው ሂደት አለው።።**
- ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- በተመስጥኦ ማንበብ
- ተዛማጅ ፅሁፎችን መመልከት
- ግለምዘና ማድርግ
- ግለምዘና ማለት ከጥናት በኃላ ጥያቄዎችን በመስራት የተረዱትን ፍሬ ነገር መከለስ።

